# አዲስ አበባ

የጣይቱ የእውነት ሕልሟ የምኒልክ እንቦቀቅላ፣
የመ ጤ ፍሬ ችግኝ ባሕር ዛፏን በዙሪያ አብቅላ፣
የአፍሪካ እምብርት ንኝ ብላ ኮርታ፥ የመሰብሰቢያ ዳስ ጥላ፣
ፖለቲከኛ ለማኝ ላባደር ሠራተኛውን ፈልፍላ፣
    አሁንም አለች መኖር ካሉት፥ ስንቱን ጎበዝ አስኮብልላ።
    አዲስ አበባ የትላንቷ ፥ አዲስ አበባ የሁሉ አድባር፣
    ወና ሜዳው ጫ ካው ጎጥሽ ፍንፍኔ ይባል እንዳልነበር፣
    ያኔ በጠዋቱ የምኒልክ ጦ ር ሲሰፍር፤
ገና ያኔ የፈረንሳይ ባቡር ሳይገባ ፦ አውሮፕላን ሳይዳስስሽ፣
ጋሪ ሳይሽከረከር መኪና ሳይፈነጭብሽ፣
ኩርኩር ሳትጀምር እግረኛ ፈረሰኛ ሳይዳምጥሽ፤
ያኔ እኮ ነው የምለው የነጭ ሰላቶ ቆሻሻውን ሳይጥልብሽ፤
የቢኖ ጠርሙ ስ ሳይሰብርብሽ፥ ወደል አይጥ ሳይለቅብሽ።
    ያኔ በልጅነትሽ የዛን ጊዜ አዲስ አበባ፣
    ጠረንሽ ሳይለወጥ ሙ ናሽ መ ቀመ ቅ ሳይገባ፤
ከሶሪያ ነጋዴ ከአርመን ሽቃጮ ች ትምክህት፣
ከቱርክ ቸርቻሪ ከግብጥ ጳጳሳት በፊት፤
ቢትወደድሽ ፊት አውራሪሽ በዋርዳ ሰጋር በቅሎ፤
ወርቀ ዘቦ መደላድል ከግላሱ አናት ጥሎ ፤
ፈረሱን በነሃስ በብር አሽሞንሙ ኖ፦
ካባ ለብሶ ነጠ ላ አደግድጎ፥ እንደጉብዝናው  ተገንኖ።
    ያን ጊዜ ባፍላነትሽ ፦ ያኔ በልግነትሽ፤
    ያኔ በሙ ሽራነት ፦ ያኔ በጫ ጉላነትሽ፤
ያኔ ያኔ ! ! ! ! !

አዲስ አበባ አዲስ መንደር፣
አዲስ አበባ አዲስ ሰፈር፤
ድንበርሽ ሳይታወቅ ገና በካሬ ሳይመ ተር፤
ከንቲባ ሳይሾምብሽ ቁጥቋጦ ሽ ሳይመ ነጠ ር።

*እጅ መንሻ ሳትለምጂ፣*
*አራዳ ኡላ ሳትወ ልጂ።*
*ያኔ በድንግልናሽ፣*
*ሳይጠ ፋ ለዛ ሙ ስናሽ፤*
*ቦሌ ሳይመ ነጠ ር፦ አስፋልቱ ሳይነጠ ፍ፤*

*ኮፍያ ደፊ ጦር ዘበኛ ሳይሰለፍ፣*
*ተማሪ ሹራብ ሲሸለም የዱቄት ወተት ሲታደል፤*
*ወንጂ ስኳር ለላሙ ና ለወጣቱ ሲከፋፈል።*

*መ ርካቶ ነጋዴሽ ሲፈለፈል፦ ገበያ አዳራሽሽ ሲሰፋ፣*
*የማሞ ካቻ አውቶብ ስ ሲያናፋ።*
*ሚ ሊቼንቶ ሴቼንቶ ፊኃት መንገድ ሲያቀና፤*
*ያኔ ነው የምልሽ ገና ወገብሽ ሳይጠ ና።*

በኋ ላማ ! ! ! !

የልጅ ነት ልጅሽ አድጎ እንደ ቡሄ ሆያ ሆዬ፤
እንደመ ስቀል አበባየሆይ ተው ስማኝ አገሬን ሲዘምር፤
ፋኖ ተሰማራን እያቅራራ የትግል ሀሁን ሲጀምር፤
የካሳንችስ የለገሃር ፤ የአራት ኪሎ የዮሃንስ፤
የአባ ኮራን የጉለሌ ለመ ርካቶ ሁሉ ጥንስስ፣
የቀበና የአቧሬ የአፍንጮ በር ሁሉ ወጣ ት ድግስ፤
የእንጦጦ ው ቤ ሰፈር የሸሮ ሜ ዳ ትርምስ፣
የለገሃር የመድሃኒአለም የቀጨ ኔ የጠ ዋት ጭ ስ።
የነፋስ ስልክ የኮልፌ የቦሌ የስድስት ኪሎ፤
ልጅ አዋቂው ተሰብስቦ መ ሬት ላራሹ ብሎ፤
ጆሊ የነበር ተለውጦ ቦልቧላ ሱሪውን ቆራጣ ቀሚሱን ጥሎ፤
ላይደነክር ተገዝቶ በአብዮት ስም ምሎ።
በአሸሼ ገዳሜ ምትክ የትግሉ ነው ሕይወቴን ዘምሮ፤
በፍልሚ ያው አምኖ በትግል ገመድ ተቋጥሮ።

ያንንማ ታሪክ አይረሳው ! ! ! ! !

ሬሳ ሲሸጥብሽ ሰው እንደ ውሻ ሲጣልብሽ፤
የደርግ ፋሽዝም ሲነግስብሽ፤
ወጣት ልግሽን ሲያርድብሽ፤
ያኔ ሰው የረከሰበት ሰአት ፣

የተቃወመ ሁሉ የፋሽስት ጥይት ሲጋት፤

ጣረ ሞት ግቢሽን ሲሞላት፤
መንግድሽን ሬሳ ሲሞላት፣
ማለፍ አይቀር አሳለፍሻት።

ዛሬም እልፍ አእላፍ አስተናግደሽ፣
በሰቆቃሽ ላይ ሰቆቃ ጥለሽ፣
የትላንትናውን ለመ ርሳት ዳንኪረኛ ዘፋኝ ቀጥረሽ፤
ወጣ ት ኮማሪቶች አስመ ርቀሽ ፤
በችግርሽ መ ቀነት ታጥረሽ፤
 ዛሬም የሰራሽው ፈራርሶ፣
 የቤትሽ ጣራው አፍስሶ፤
መ ንገድሽ እንደ ጅብ ወጥመድ ከዚህ ከዚያ ተሰርጉዶ፣
ቆሻሽ ተቆልሎ እንደ ደገኛ ነዶ፤
ዛሬማ ዛሬማ ！！！！！
ገመ ምተኛ ነሽ እማማ ！！！！

አዲስ አበባ አይ አዲስ አበባ ！！！！！
የዮፍታሄ ውብ አሸከር ቀዘባ！！！！
አዲስ አበባ።

ተኮላ መ ኮንን
DALLAS, SEPTEMBER 30
1994